# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት
## ልሣነ - ሕግ ጋዜጣ
## LISSANE HIG GAZETA OF
## THE BENISHANGUL GUMUZ REGIONAL STATE

| | | |
|---|---|---|
| 16ኛ ዓመት ቁጥር 87<br>አሶሳ ሐምሌ 2002 | በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ<br>Proclaimed Under Auspices Of Benishangul<br>Gumuz Regional State Council | 16th year N0.87<br>Assosa July, 2010 |

## አዋጅ ቁጥር 87/2002

## በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የመንገድ የትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ

**መግቢያ፣**

በክልሉ ውስጥ በመንገድ ትራፊክ አደጋ ምክንያት በሰው ሕይወት፣ አካል ንብረትና ኢኮኖሚው ላይ እየደረሰ ያለውን የጉዳት መጠን ደረጃ በደረጃ መቀነስ እንዲቻል በመታመኑ፣

ከመንገድ ትራፊክ ደህንነት ግንኙነት ያላቸው የክልሉ አካላት የተቀናጀ እቅድ የሚያወጡበትና ተግባራዊነቱን የሚከታተሉበት አመቺ የጋራ መድረክ ማቋቋም በማስፈለጉ፣

የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት መቋቋም የሰው ኃይልን ገንዘብንና መገልገያ መሣሪያዎችን በተደራጀና በተቀናጀ መልክ በመጠቀም ለትራፊክ አደጋ መቀነስ የሚረዱ እርምጃዎችን ለማካሄድ የሚያስችል በመሆኑ፣

የመንገድ ትራፊክ አደጋ ለመቀነስ በተለያዩ አካላት በተናጠል ሲሰራ የነበረውን የሥራ ድግግሞሽ በመቀነስ ውስን ሀብቶችን ውጤታማ በሆነ መልክ በመጠቀም የትራፊክ ደህንነት እየተሻሻለ እንዲሄድ የሚያደርግ መሆኑ ስለታመነበት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 49/3/1/ መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

### አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 87/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ

1. "ምክር ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በክልሉ ውስጥ በክልል፣ በዞን፣በወረዳ በከተሞችና በቀበሌ የተቋቋመው የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት ማለት ነው፡፡

## Proclamation No 87/2002

## THE BENISHANGUL GUMUZ REGIONAL STATE ROAD SAFETY COUNCIL ESTABLISHMENT PROCLAMATION

### INTRODUCTION

Where as, it is necessary to reduce step by step the level of damages caused by road traffic accident to human life, body property and the economy in the Benishangul Gumuz regional State.
Where as it is found necessary to create a conducive forum where by organs of the regional state that have work relation ship directly or indirectly to road coordinated plan and follow up its implementation.

Where as, the establishment of the road traffic safety council shall enable to take measures that could reduce traffic accidents by utilizing human, financial and material resources in organized and coordinated manner.

Where as, it is believed that, traffic safety will be improved by reducing the redundant activities undertaken to reduce road accident by various organization independently and by effecting utilizing the limited resources.

**Part one**

**General**

### Article 1. Short title

This proclamation may be cited as "The Benishangul Gumuz Regional state road safety council establishment proclamation No 87/2010"

### Article 2. Definition

In this proclamation

1. "Council" shall mean the council established by this proclamation for road traffic safety at the regional, Zonal, Woreda and towns in the region.

2. ‹‹ማስተባበሪያ ጽ/ቤት›› ማለት በዚህ አዋጅ በክልሉ ንግድ ትራንስፖርትና እንዱስትሪ ቢሮ ስር የተቋቋመ ጽ/ቤት ነዉ፡፡
3. "የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ተግባር" ማለት የመንገድ ትራፊክ አደጋን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚደረግ እንቅስቃሴና ከዚህ ጋር ግንኙነት ያለውን ተግባራት ሁሉ ያጠቃልላል፡፡
4. "ክልል" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ነው፡፡
5. "ትራፊክ" ማለት በማንኛውም መንገድ ላይ አንድ ወይም ብዙ ሆነው የሚተላለፉ እግረኞች እንስሳት እና ተሽከርካሪዎች ናቸው፡፡
6. "መንገድ " ማለት ተሽከርካሪዎችና እግረኞች በተለምዶ የሚጠቀሙበት ማናቸውም ጉዳና ወይም መንገድ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

መቋቋም አላማና የምክር ቤቱ ልዩ ልዩ አካላት

**አንቀጽ 3. መቋቋም**

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት ከዚህ በኋላ ምክር ቤት እየተባለ የሚጠራው የክልሉ አስፈጻሚ አካል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

**አንቀጽ 4. ዓላማ**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል

1. የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም በክልሉ የትራፊክ አደጋን በመቀነስ በዚህ ምክንያት በሰውና በንብረት ላይ እየደረሰ ያለውን የጉዳት መጠን ለመቀነስ
2. ከመንገድ ትራፊክ ደህንነት ጋር በተያያዘ በሕግ አስፈጻሚነት ሥራ ላይ የተሰማሩ የክልሉ አካላት የተቀናጀ የሥራ ግንኙነት እንዲኖራቸው የማድረግ

2. “coordination office” shall mean the office established by this proclamation and accountable to bureau of trade transport and industry
3. “Road safety” shall mean the movement of road users without accident of to sage use them from greater damage it there is any activity related to it
4. “Regional state” shall mean the Benishangul Regional state.
5. “Road users of traffic” shall mean the pedestrians animals or vehicles using the roads.
6. “Road” shall mean any road which is commonly used by vehicles and pedestrians.

## Part two

Establishment objectives and different organs of the council

**Article 3. Establishment**

The Benishangul Gumuz Regional state road safety council here in after referred to as the council is here by established as an executive organ of the regional government by proclamation.

**Article 4. Objective**

The council shall have the following objectives.

1. Reduce the degree of damages on human life and property caused by traffic accident utilizing various means in the region.
2. Cause law enforcement organs involved in road traffic safety activities to establish coordinated working relation ship.

3. በክልሉ ውስጥ በቂ የትራፊክ አደጋ የቅድመ መከላከልና አስተማማኝ የአደጋ እርዳታ ያለው የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ሥርዓት ማደራጀት

## አንቀጽ 5. የምክር ቤቱ አደረጃጀት

1. ምክር ቤቱ አግባብነት ያሉትን የሚከተሉትን የክልሉ አካላትን በአባልነት የሚይዝ ይሆናል፡፡

   ሀ/ የንግድ ትራንስፖርትና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ ሰብሳቢ

   ለ/ የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ፀሐፊ

   ሐ/ የንግድ ትራንስፖርት እንዱስትሪ ፈቃድ ምዝገባ ጥናት ማስፋፊያ መምሪያ ኃላፊ አባል

   መ/ የገጠር መንገዶች ባለስልጣን ሥራ አስኪያጅ አባል

   ሠ/ የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ኃላፊ አባል

   ረ/ የአሶሳ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሹም አባል

   ሰ/ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አባል

   ሸ/ የክልሉ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊ አባል

   በ/ የፍትህ ቢሮ ኃላፊ አባል

   ተ/ ከሕዝብ ትራንስፖርት ማህበራትና ከጭነት ማመላለሻ ማህበራት በምርጫ የተወከሉ 3 ሰዎች አባላት

   ቀ/ የማስታወቂያ ባህል ቱሪዝምና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ አባል

2. የምክር ቤቱ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በንግድ ትራንስፖርትና ኢንዱስትሪ ቢሮ ውስጥ ይሆናል፡፡

3. ምክር ቤቱ በንግድ ትራንስፖርትና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ የሚመራ ይሆናል፡፡

4. ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ የሆነ አንድ አስተባባሪ እና ሌሎች ባለሙያዎች ይኖሩታልሰ፡፡

3. Organize modern efficient road safety system that has sufficient traffic accident prevention and reliable emergency services.

## Article 5. Organization of the Council

1. The council shall have the following appropriate organs of the regional governments.

   a. TRADE TRANSPORT AND INDUSTRY/ bureau head chairman
   b. The regional police commission commissioner Secretary
   c. TRADE TRANSPORT AND INDUSTRY/ license registration department head secretary
   d. Rural roads authority manager member
   e. The regional health bureau head member
   f. Assosa town municipality head member
   g. Education Bureau head member
   h. The regional works and urban development bureau member
   i. Justice bureau head member Three delegated persons from transportation unions members.
   j. The regional information culture. Tourism ,and Social affairs bureau head member

2. The coordination office of the council shall be located with in the Trade transport industry bureau

3. The council shall be lead by the head Trade Transport Industry bureau

4. The office shall have the necessary professionals and coordinator who is accountable for the council.

## ክፍል ሶስት

### አንቀጽ 6. ተጠሪነቱ

የምክር ቤቱ ተጠሪነት በየደረጃዉ ላለዉ ካቢኔ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 7. የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

1. የክልሉን የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ችግሮች ደረጃ በደረጃ የሚቀንሱበትንና በዘላቂነት መፍትሔ የሚያገኙበትን ሁኔታ በተመለከተ በጥናት ላይ የተመሠረተ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅድ በማውጣት ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት አማካኝነት ተግባራዊ እንዲሆኑ ያማክራል፡፡
2. የትራፊክ አስተዳደርና የቁጥጥር ብቃት በክልሉ ውስጥ ማጉልበት እንዲቻል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስልጠና የሰው ኃይል ዘመናዊ የቴክኒክ መገልገያዎች በአስፈላጊው መጠን የሚገኙበትንና ሥራ ላይ የሚውልበትን መንገድ ለሚመለከታቸው አካላት ያማክራል፡፡
3. በክልሉ ውስጥ በመንገድ ትራፊክ ደህንነት ተግባር ላይ በተሰማሩ አካላት መካከል የሥራ ትብብር እንዲዳበር ምቹ ሁኔታን በመፍጠርና ሥራዎች በቁጠባና እርስ በርሱ በሚደጋገፍበት አኳኋን እንዲካሄዱ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡
4. በክልሉ ውስጥ የሚዘጋጁ የአሽከርካሪዎች ስልጠናና ችሎታ መመዘኛ ፈተናዎች ተፈትኖ የብቃት ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑና የማስፈጸም ኃላፊነት ላለባቸው አካላት አስፈላጊውን ምክርና ድጋፍ ያደርጋል፡፡
5. በተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ብቃትና ደረጃ በተመለከተ የወጡ መመዘኛዎች በክልሉ ውስጥ በትክክል ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚመለከታቸውን አካላት ያማክራል፡፡

## Part Three

### Article 6. Accountability

The Council shall be accountable to the cabinet each level.

### Article 7. Powers and function at the council

The council shall have the following powers and function to

1. Prepare short medium and long term plans based on studies to reduce and to provide lasting solution to road safety problems advice the implementation at the same to the appropriate organs.
2. Provide advice concerning the provision and utilization at trained human resources and technical equipments in a reasonable quantity in order to enhance traffic administration and control competency.
3. Provide advisory services to create conducive environment for organs operating with in the regional state concerning road traffic safety activities to cooperate and support each other and function economically.
4. Provide the necessary advises and assistance to those implementing organs to ensure that drivers training and competently tests are in accordance with the required standards.
5. Counsel the appropriate organs or the proper application on of technical competency and standards of rechecks in the region

6. በክልሉ ውስጥ የመንገድ ቅየሣ የግንባታና የተሽከርካሪ የጥገና ሥራ እንዲሁም ከዚሁ ጋር በተያያዘ የተለያዩ አገልግሎት መስመሮች የመዘርጋት እቅድ ተገቢውን የደረጃ መመዘኛ ባሟላ መከናወኑን በማረጋገጥ ስልጣን ላላቸው አካላት ምክር ይሰጣል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የሚያጋጥሙ ክፍተቶችን ለመሙላት በሚመለከታቸው አካላት አማካኝነት አዲስ ሕግ እንዲወጣ ሃሣብ ያቀርባል።

7. በሥራ ላይ ያለውን የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ነክ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን እንዲሁም በጥናት ላይ በመመሥረት ሕጐች የሚሻሻሉበትና እንደ አስፈላጊነቱም አዳዲስ ሕጐችን የሚወጡበትን ሃሣብ ያቀርባል።

8. የክልሉ ነዋሪ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ግንዛቤ እየዳበረ እንዲሄድ ትምህርትና ቅስቀሳ የሚሰጥበትን ሁኔታ በማጥናት ለሚመለከተው ክፍል ያቀርባል።

9. ሌሎች የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ተግባሮች በተመለከተ ሲጠየቅ የምክር አገልግሎት ይሰጣል።

**አንቀጽ 8. ስለ ምክር ቤቱ ስብሰባ**

1. ምክር ቤቱ በዓመት አራት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሄዳል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ምክር ቤቱ ስብሰባ በማንኛውም ጊዜ ሊጠራ ይችላል።

2. ማንኛውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ምልዓተ ጉባኤ ከጠቅላላ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ይሆናል።

3. በምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ ውሣኔዎች የሚተላለፉት ከግማሽ በላይ በሆነ የድጋፍ ድምጽ ይሆናል። ድምጽ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ ግን ሰብሳቢው ባለበት ወገን የተደገፈ ሃሣብ የፀና ይሆናል።

6. Provide advise to ensure the survey designing building and maintenance of road as well as in relation with it the land used and plan of installation of different service lines are sane with in the required standards initiate the enactment of hew laws to fill gaps as may be necessary.

7. Counsel the appropriate organs that ensure the implementation of road traffic safety proclamations regulations and based up on study provide opinion for amendment of laws and enactment at new laws.

8. Develop mechanisms to enhance the awareness of residents concerning road traffic safety.

9. Provide advises concerning other road traffic safety activities wale required.

Article 8. Meeting at the Council

1. The Council shall have a regular meeting every quarter of a year. Earth ordinary meeting may be called as may be necessary.
2. Their shall be forum where more than half of the members of the council are present in the meetings.
3. A decision in the council shall be passed by majority vote. The chairman shall have a casting vote in case where there is a tie.

4. ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፡፡

**አንቀጽ 9. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ስልጣንና ተግባር**

የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. በምክር ቤቱ የሚተላለፉ ውሣኔዎችና መመሪያዎች ያስፈጽማል፣
2. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን በተመለከተ መረጃዎችን ይሰበስባል ያጠናክራል እንዲሁም ይተነትናል፡፡
3. በጥናት ላይ የተመሠረቱ ለመንገድ ትራፊክ ደህንነት ችግሮች መቃለል የሚረዱ የመፍትሔ ሃሣቦችን ይሰጣል፡፡
4. ዓመታዊ የሥራና የበጀት እቅዱን ለምክርቤቱ ያቀርባል፡፡ ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፣
5. የሥራ ክንውንና የሂሣብ ሪፖርት በዓመት አንድ ጊዜ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ምክር ቤቱ የሥራ ክንውንና የሂሣብ ሪፖርት በማንኛውም ጊዜ እንዲቀርብለት ሲጠየቅ ጽ/ቤቱ ያቀርባል፡፡

4. The council shall have its own meeting procedures.

**Article 9. Power and functions of road traffic safety coordination office**

The office of road and safety coordinator shall have the following powers and function

1. Enforce the decisions and directives of the counsel.
2. Collect, organization and analyses road traffic related data by way of establishing relation ship with relevant organs.
3. Provide solutions based on studies that assist to improve road traffic safety.
4. Submit its annual plan and bud get to the council implement same up on approval.
5. Submit activity and fiscal report annually to the council, however submit same when ever the council demands so.

## አንቀጽ 10. የአስተባባሪው ተግባርና ኃላፊነት

የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማስተባበሪያ አስተባባሪ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ሲሆን በንግድ ትራንስፖርትና ኢንዱስትሪ ቢሮ አቅራቢነት በምክር ቤቱ የሚመደብ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባሮች ያከውናል፡፡

1. አስተባባሪዉ የማስተባበሪያ ጽ/በቱን ሥራ በኃላፊነት ይመራል ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ያቀርባል እንደዚሁ በንግድ ትራንስፖርት ኢንዱስትሪ ቢሮ ምክር ቤቱን ያማክራል፡፡
2. አስተባባሪዉ በመንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ሕግ መሠረት የሚተዳደሩ ባለሙያዎች እንደአስፈላጊነቱ እንድኖሩት ያደርጋል፡፡
3. በማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ስም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የእለት ተእለት የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፡፡
4. በማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ስም እቅድና ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፡፡ በምክር ቤቱ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
5. በምክር ቤቱ ወይም በንግድ ትራንስፖርት ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 11. የዞን ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት

ሀ/ የዞን ንግድ ትራንስፖርት ኢንዱስትሪ ጽህፈት በት ኃላፊ ሰብሳቢ
ለ/ የዞን ትራፊክ ክፍል ኃላፊ ፀሀፊ
ሐ/ የዞኑ ፖሊስ ጽ/ቤት አዛዥ አባል
መ/ የዞኑ የጤና ጥበቃ ደስክ ኃላፊ አባል
ሠ/ የዞኑ ትምህርት ደስክ ኃላፊ አባል
ረ/ ከትራንስፖርት ማህበራት በምርጫ የሚቀርቡ 4 ሰዎች አባላት

## አንቀጽ 12 የከተማ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት

ሀ/ የከተማ ከንቲባ ሰብሳቢ

ለ. የንግድ ትራንስፖርት ኢንዱስትሪ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ፀሀፊ

ሐ. የከተማ አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ አባል

መ. የከተማው ፖሊስ አዛዥ አባል

ሠ. የከተማው ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አባል

ረ. የከተማው ት/ቤቶች ጽህፈት ቤት ኃላፊ አባል

ሰ. ከሕዝብ ትራንስፖርት ማህበራት በምርጫ የሚቀርቡ 2 ሰዎች አባላት

ቀ. የከተማው ትራፊክ ክፍል ኃላፊ አባል

## Article 10 Powers and function of the coordinator.

The coordinator shall be assigned by the council up on recommendation on by the bureau head of Trade Transport Industry Bureau.

1. Direct the office of the coordination prepare plan and follow up its implementation prepare and submit report as well as a device the bureau head of Trade Transport Industry bureau.
2. Staff and regulate the coordination office with the necessary civil servant.
3. Represent the office in its day to day function before third party.
4. Prepare the office plan, annual budget and implement same up on approval by the council.
5. Implement other activities ordered by the council or by Trade Transport Industry bureau head.

## Article 11. Zonal road safety Council

a. Zonal Trade Transport and Industry office head chairman
b. Zonal Traffic officer secretary
c. Zonal police office head member
d. Zonal health office head member
e. Zonal education office head member.
f. Four delegated persons from transportation union's members.

## Article 12. Town road safety Council

a. Town administration head chairman.
b. Trade Transport Industry office head secretary
c. Town administration manager member
d. Town police commander member
e. Town health office head member
f. Town education head member
g. Two delegated persons from transport associations member
h. Town traffic police head

## አንቀጽ 13. የወረዳ የትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት

ሀ. የወረዳው መስተዳደር ምክር ቤት ዋና አስተዳዳሪ ሰብሳቢ

ለ. የወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት አዛዥ ፀሀፊ

ሐ. የወረዳው ፖሊስ ትራፊክ ክፍል ኃላፊ አባል

መ. የወረዳው የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራ ዴስክ ኃላፊ አባል

ሠ. የወረዳው አቅም ግንባታ ትምህርት ቤቶች ጽህፈት ቤት ኃላፊ አባል

ረ. የከተማው ቀበሌ ሊቀ መናብርት አባል

ሰ. የወረዳው ከተማ ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አባል

ሸ. የከተማ መዘጋጃ ቤት ሹም አባል

## አንቀጽ 14. የዞን የወረዳና የከተማ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የከተማውን የዞኑ እና የወረዳውን የትራፊክ ደህንነት የሥራ እቅድ በቅንጅት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡
2. ለሥራው የሚያስፈልገውን መሣሪያ በማጤን እንዲፈቀድለት በቢሮ በኩል ለምክር ቤቱ ያቀርባል
3. የምክር ቤቱን ውሣኔ በመቀበል በሥራ ላይ ያውላል፡፡
4. በክልሉ ምክር ቤት የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናወናል፡፡

## አንቀጽ 15. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት የገቢ ምንጮች

የክልሉ የመንገድ ትራፊክ ምክር ቤት የሚከተሉትን የገቢ ምንጮች የኖሩታል፡፡

1. ከኢትዮጵያ የመንገድ ፈንድ አስተዳደር ጽ/ቤት የሚመደብ በጀት
2. የክልሉ መንግስት በሚወሰነው መሠረት ሌሎች ከትራፊክ ደህንነት ጋር ተያያዥነት ያላቸውና በሌሎች አካላት ስልጣን ሥር ያልተሸፈኑ ገቢዎች
3. በክልሉ መንግስት ከሚመደብ በጀት

## Article 13. Woreda level road safety Council

a. woreda administrative head chairman

b. Woreda police commander secretary

c. Woreda traffic police head member

d. Woreda micro and small scales trade desk Member

e. Woreda education office head member

f. Town kebele chair men member

g. Worda health office head member

h. Towen municipality head member

## Article 14. Powers and function of Zone, woreda and town road safety Councils

a. The council shall prepare the zonal or woredas round safety plan with coordination

b. Observing necessary materials needed for the work and appeal to the council through Trade Transport Industry bureau

**c.** By recalling the decisions of board apply it in practice.

**d.** Shall perform other activities ordered by the regional council.

## Article 15. Sources of income

The regional road safety council shall have the following source of incomes

1. Budget assigned by the Ethiopia road fund administration secretary
2. From any assistance in kind or in cash from different sources and from other income of traffic safety which don't fall under the authority of other bodies depending on the decision of the regional government.
3. Budget assigned by the Regional government.

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 16. ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ሕግና ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### አንቀጽ 17. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስችለውን ደንብ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያወጣል፡፡
2. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን የክልሉ ንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ ያወጣል፣

### አንቀጽ 18. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ፀድቆ በልሳነ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

መጋቢት -------- ቀን 2002 ዓ.ም.

አህመድ ናስር አህመድ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዚዳንት

## Part four

## Miscellaneous provisions

### Article 16. Inapplicable laws

Any law or practices that are in consistent with this proclamation shall not be applicable.

### Article 17. Power to issue directives

1. The administrative council may issues regulation **to** implement this proclamation
2. Trade, Industry Transport Bureau may issue directives in order to implement this proclamation

### Article 18. Effective Date

**This proclamation shall be effective as of the day it is published in the Lisane Hig Gazeta of the Regional Council up on approved.**

**Done at Assosa, this----day of March, 2010**

**Ahmed Nasir Ahmed-**

**President of Benishangul Gumuz Regional State**